## ሁላችንንም ይመለከታል፡ ለዓለምዓቀፉ ፈተና እንዘጋጅ

በእንዲህ አይነቱ የቀውስ ወቅት ምርጡ ማንንታችን ይገለጻል። በዚህ የወረረሽኝ ወቅት የጤና ባለሞያዎች ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ህምመተኞችን ለማትረፍ ሲረባረቡ እየተመለከትን ነው። ወጣቶች ሰብሰብ ብለው ምግብ እና ሌሎች አቅርቦቶችን በበጎ ፈቃደኝነት ሲያቀርቡ እንዲሁም አምራች ኢንደስትሪዎች በበኩላቸው ደግሞ በአፋጣኝ አስፈላጊ የህይወት አድን መሳሪያዎችን ማምረት ላይ እየተረባረቡ ይገኛሉ። በዚህ ፈታኝ ወቅት እየተመለከትን የምንገኘው መተሳሰብ ተስፋን የሚያጭር እና የሰው ልጅን የመቻል አቅም የሚያሳይ ነው።

ይሁንና ኮቪድ 19 ሌላም ያሳየን ነገር አለ፡ እርሱም በመካከላችን ያለውን የኑሮ ሁኔታ ልዩነት ነው። በአለም ላይ የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቀን ገቢ የነበራቸው ሰዎች በቤታቸው ውስጥ ለመቆየት ይቸገራሉ።

በተጠጋጋ እና ከደረጃ በታች በሆኑ የመኖሪያ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ማህበራዊ ፈቀቅታን ተግባራዊ ማድረግን ፈፅሞ እንዳይቻል ያደርገዋል። በድህነት ውስጥ የሚኖሩ የማህበረሰቡ አባላት በዚህ የወረርሽን ወቅት ለቫይረሱ ተጋላጭነታቸው ፤ ይህ ነገር ካለፈ በኋላ ደግሞ በኢኮኖሚው በኩል በእጅጉ ተጎጂ እንደሚሆኑ ይገመታል።

በዚህ በፈጣን ሁኔታ እየተስፋፋ በመጣው ማህበራዊ ቀውስ ምክንያት ሁለት ነገሮች ግልፅ ናቸው። የመጀመሪያው ለችግሩ ተጋላጭ የሆኑትን ለመታደግ መረባረብ ሲሆን ሁለተኛው እና አሁኑኑ መተግበር የሚገባን ጉዳይ ደግሞ ቤተሰብን እና ማህበረሰቡን ከዚህ ችግር በኋላ መልሶ ለማቋቋም የሚያግዙ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን መስራት ነው። ይህንን ደግሞ ቁልፍ የሚባሉ ተቋሞቻችንን በማጠናከር ማሳካት ይቻላል። እነዚህ ተቋማት እና ከባቢያቸው ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አሁንም ሆነ ለወደፊት ጠንካራ መሰረቶች ናቸው።

ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን በአፍሪካ ሚሊዮኖችን እና በእነሱ ዙሪያ ያሉ ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ያደረገ የቢሊዮን ዶላሮች መዋዕለንዋይን ከፈረንጆቹ 2008 ጀምሮ ሲያፈስ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ወጣት አፍሪካውያን እና ካናዳውያን በማዞር ወጣቶቹ ትምህርት፣ ክህሎት እና የተሻለ ስራ እንዲያገኙ በማገዝ ላይ ይገኛል።

ተልዕኳችንን ለማሳካትም አኮኖሚን ከሚያሽከረክሩት ዩኒቨርሲቲዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ስራ ፈጣሪዎች፣ ማህበረሰብ እና ወጣት ማህበራት እና የመንግስት ተቋማት ጋር ጠንካራ ጥምረት ፈጥረናል። ምንም እንኳን ኮቪድ19 የተሻለ ስራን ለመፍጠር አስቸጋሪ ቢሆንብንም ፣ ፈጽሞ አያቆመንም። የኢሌልቪ እና ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ስኮላር ፕሮግራሞች እንዲሁም ያንግ አፍሪካ ዎርክስ ስትራቴጂዎቻችን አሁንም የሚቀጥሉ ይሆናል።

ወጣቶቻችን የተሻለ ትምህርት፣ ክህሎት እና ስራ የሚያገኙባቸውን መንገዶች እንዲያገኙ ከአጋሮቻችን ጋር አሁንም መስራታችንን የምንቀጥል ይሆናል። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ወረርሽኙን ለመከላከል ከሌሎች ጋር በመተባበር የበለጠ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰቡን ክፍሎች መጠበቅ ይገባናል።

ዛሬ የማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ከቪድ19 የመልሶ መቋቋም እና መመከት ፕሮግራምን በይፋ ጀምረናል። ይህ ፕሮግራም ሁለት ዋና ዋና አላማዎች ሲኖሩት ፤ አንደኛው፡ ለህክምና ባለሞያዎች እና ለሌሎች ወረርሽኙን ለመከላከል ከፊት ለሚሰለፉ ባለሞያዎች የህክምና ቁሳቁሶችን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ እና ለተማሪዎች የአስቸኳይ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ የአሁኑን እና የወደፊቱን ችግሮች የመፍታት አቅም ላላቸው እና ኢኮኖሚው በፍጥነት እንዲያገግም ለሚያግዙ ፕሮጀክቶች ድጋፋችንን በእጥፍ ማሳደግ ይሆናል። በተለይም በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በትኩረት የምንሰራ ይሆናል ፡-

1) **ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦትን መጨመር** እነዚህ ተቋማት አሰራራቸውን ወደ ዲጂታላይዜሽን እንዲያሳድጉ ፣ የኮቪድ 19 የኢኮኖሚ ተጽዕኖን ተቋቁመው እንዲቆዩ እና ምናልባትም የጤና ስርዓቱን የሚያግዙ ምርቶችን እንዲያመርቱ እና እንዲያቀርቡ ማገዝ።

2) **የኢንተርኔት ትምህርት እንዲኖር ማስቻል** - በወረርሽኙ ምክንያት ትምህርታቸው የተቋረጠባቸው ወጣቶችን ለማገዝ ሲሆን ይህም ከትምህርት ተቋማት ጋር የሚሰራ ይሆናል። በሂደቱም ተቋማቱ ተማሪዎቻቸው ለመቆጣጠር፣ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ እና ፈተና እንዲወስዱ የሚያስችላቸው ሲሆን ይህ አይነቱ እርምጃ የትምህርት ተቋማትን ለመሰል ቀውሶች እንዲዘጋጁ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ሁኔታን እስከወዲያኛው የሚቀይር ነው።

3) **ዲጂታል መፍትሄዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማገዝ -** መሰረታዊ ለሆኑ እንደ የፋይናንስ ስርዓት፣ የምግብ ምርት እና አቅርቦት፣ ቤቶች እና ግንባታዎች፣ ትራንስፖርቴሽን እና ማጓጓዝ፣ የህብረተሰብ ጤና መጠበቂያዎች ምርት እና አቅርቦት ላሉ አገልግሎቶች ማደግ የዲጂታል ስርዓቱ ጥሩ በሆኑባቸው አካባቢዎች ከሌላቸው አንጻር የተሻሉ እንደሆኑ ይታወቃል።

እነዚህን ተግባራት በመፈጸም እና የተለያዩ ተቋማትን አቅም በማጠናከር ይህንን ዓለምአቀፍ ወረርሽኝ መመከት እንችላለን። በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ ወረርሽኝ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመከላከል እና ወደ ጤናማነት ለመመለስ ህብረተሰቡ ተነሳሽ ሆኖ ፣ ተቋማትም ዝግጁ ሆነው ለማየት እንፈልጋለን።

ለጊዜው ከዚህ ቀውስ እንዴት እንደምንወጣ የሚጠቁም ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ፍኖተ ካርታ የለንም ፤ ነገር ግን አሁን የምናከናውናቸው ተግባራት ከኮቪድ19 በኋላ የሚኖረውን የዓለም ሁኔታ ይወስነዋል። ይሄ ቀውስ እያስተማረን የሚገኘው ምን ያክል አንዳችን ለአንዳችን የተሳሰርን መሆናችንን እና በጋራ የምንደርጋቸው ነገሮች ምን ያክል ጥንካሬ

እንዳላቸው ነው። በየግላችንም ቢሆን የቫይረሱን ስርጭት ለማቆም የአቅማችንን ያህል ማድረግ እንችላለን። በጋራ የኮቪድ19 የኢኮኖሚ ቀውስን ለመወጣት የሚያስችል ኃይል ይኖረናል።

ዓለማችንን ጠንካራ ፣ ፍትሃዊ እና ለሁላችንም ደህንነት የምትመች አድርገን በድጋሚ መገንባት እንችላለን። ምክንያቱም ጉዳዩ ሁላችንንም ይመለከተናልና።

***ሪታ***

**የማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ፕሬዝዳንት እና ዋና ስራ አስፈጻሚ**